## ከነባሩ የዳያስፖራ መኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ አሰጣጥ መመሪያ ማሻሻያ የተደረገባቸው ነጥቦች

### መግቢያ

በውጭ አገራት ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በማህበር ተደራጅተው የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታ ለማግኘት የሚያስችላቸው መመሪያ በ2007 ዓ.ም በመስተዳድር ም/ቤቱ የወጣ ቢሆንም እስካሁን ድረስ ጥያቄ የቀረቡና የመመሪያውን መስፈርት ያሟሉ ዳያስፐፖራዎች የሉም፡፡ በውጭ አገራት ለሚገኙት 54 ሚስዮኖች እና ለዳያስፖራው በመመሪያው ላይ ግንዛቤ ቢፈጠርም በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን የቤት አይነቶች የግንባታ ወጭ ቅድሚያ 100% ለመክፈልና በዝግ አካውንት በባንክ ለማስቀመጥ አቅማቸውን ያላገናዘበ መሆኑን በመግለጽ ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም፡፡ የክልልና የፌደራል ከፍተኛ አመራሮች ወደ ውጭ አገራት ሄደው በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ከዳያስፖራው ጋር ሲወያዩ አንዱ የሚነሳው የመልካም አስተዳደር ጥያቄ መመሪያው የዳያስፖራውን አቅም ያላገናዘበ ስለሆነ እንዲሻሻል አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ስለሆነም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየትና ግብዓት በመውሰድ የማሻሻያ ሀሳቦቹን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

### የተሻሻሉ አንቀጾች

1.“ቢሮ” **ኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ የሚለው** የክልሉ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ በሚል ተስተካክሏል፡፡

ሀ) እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነና በህግ ወይም በፍርድ ያልተከለከለ፤

ተ) በመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታውን ግማሽ ወጭ በውጭ ምንዛሪ ከፍሎ በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያደረገ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ደረሰኝ ቅጂ ማቅረብ የሚችል፤

ቸ) ከዚህ በላይ በፊደል ተራ ቁጥር “ተ” መሰረት ገቢ ከተደረገው ግማሽ የግንባታ ወጪ ውስጥ 25 ከመቶ የሚሆነውን በምዝገባ ወቅት በሚኖርበት አገር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በኩል ሂሳብ በመክፈት አስቀድሞ ያስቀመጠና በአባልነት የተመዘገበበት የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ለግንባታ የተዘጋጀውን የከተማ ቦታ በሚረከብበት ጊዜ ደግሞ ቀሪውን 25 ከመቶ አጠናቆ በመክፈል የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ዝግጁ የሆነ ፤

መ) በተመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት ከግንባታው ጠቅላላ ወጪ ውስጥ 50 ከመቶ የሚሆነው በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ በወካዩ ስም በውጭ ምንዛሪ ገቢ የተደረገ ስለመሆኑ የሚያሣይ ደረሰኝ የተረጋገጠ ቅጅ፤

ሰ) የተመረጠው ታውን ሀውስ (G+2) ሲሆን፡-

I. ቤቱ ባለ 3 መኝታና የቦታው ስፋት 92 ካ.ሜ. የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ቢያንስ ብር 693,120/ ስድስት መቶ ዘጠና ሶስት ሽህ አንድ መቶ ሀያ ብር/ ይሆናል፤

II. ቤቱ ባለ 4 መኝታና የቤቱ ስፋት 100ካ.ሜ .የሆነ እንደሆነ የግንባታ ወጭው ቢያንስ ብር 912,000/ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለትሽብር/ ይሆናል።

III. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የተመለከቱት ወጭዎች ይህ መመሪያ በስራ ላይ በዋለበት ወቅት የሚታየውን የገበያ ዋጋ የሚገልፁ ሲሆን እንደየ ከተሞቹ ተጨባጭ ሁኔታና ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ዕድገት በጥናት ላይ እና በሚያቀርቡት የቤት ዲዛይን አማራጭ የተመሰረተ ማሻሻያ ሊደረግባቸው ይችላል።

4.የከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ

5. በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የዲያስፖራና የህዝብ ግንኙነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

1.በመረጠው የመኖሪያ ቤት አይነት የግንባታው ወጪ 50 ከመቶ በውጭ ምንዛሪ ተከፍሎ በአገር ውስጥ በተከፈተ የባንክ ሂሣብ ገቢ ስለመደረጉ የሚያስረዳና ከዋናው ጋር የተገናዘበ የክፍያ ደረሰኝ ቅጂ ማሳየት።

2.በተመሳሳይ ሁኔታ ከተማ ልማት ቤቶችና ኮንስትራክሽን ቢሮ በኩል ጥያቄ ሲቀርብለት በመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማኅበራት ለተደራጁ ወገኖች ገንዘብ ማስተላለፊያ የሚያገለግል ሂሣብ ይከፍታል።

3.የመጀመሪያውን ፎርማሊቲ አሟልተው 25 ከመቶ ክፍያ ያጠናቀቁና እውቅና ያገኙ ማህበራት 25 በመቶ መሬት ለማግኘት የከፈሉ ማህበራት ቁጥር ለግንባታ ከተዘጋጀው መሬት በላይ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የቦታ እደላው የየማህበራቱ ተወካዮች በተገኙበት በዕጣ ይከናወናል፤